የሰ/መ/ቁ. 37303

ጥር 26 ቀን 2001 ዓ.ም

**ዳኞች**፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጐስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

በላቸው መንሺሶ

ሱልጣን አባተማም

**አመልካች**፡- ኤ.ሲ.ዲ.አይ/ቮካ- ኢትዮጵያ - ስራጅ ዓብደላ/ጠበቃ/ ቀረበ

**ተጠሪዎች**፡- 1. ሃይደር ዓሊ
2. ሑሴን ሰዒድ ዓብደላ
3. ግርማ ሐጐስ ገ/ጊዮርጊስ
4. ሽምሰዲን መሐመድ ዓሊ
5. አርባ ሑመድ
6. ወ/ሪት ዛህራ እንድሪስ
7. መሐመድ ኢብራሂም ዑመር
8. ወንድሙ አባቡ አስማረ

} ጠበቃ አወል ሰይድ ቀረበ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ በአሰሪና ሰራተኞች መካከል የተነሣውን የስራ ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ በተጀመረበት በአፋር ብ/ክ/መንግስት በዱብቲ ወረዳ ፍ/ቤት ከሣሾች የነበሩት ተጠሪዎች ናቸው፡፡ በአመልካች ላይ ክስ የመሰረቱትም ሳይከፈል ቀርቶአል ያሉትን የበረሃ አበል እንዲከፈላቸው ነው፡፡ የወረዳው ፍ/ቤት የሁለቱን ወገኖች ክርክር ከሰማ በኋላ፣ተጠሪዎች በጠየቁት መሰረት የበረሃ አበል እንዲከፈላቸው ወስኖአል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ አመልካች ውሳኔውን በመቃወም ለክልሉ የዞን አንድ ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ በማቅረቡ ክርክሩ በድጋሚ ተሰምቶአል፡፡ በመጨረሻም ፍ/ቤቱ በወረዳው ፍ/ቤት ተሰጥቶ የነበረውን ውሳኔ ሽሮአል፡፡ ከመዝገቡ እንደሚታየው የከፍተኛው ፍ/ቤት በወረዳው ፍ/ቤት ተሰጥቶ የነበረውን ውሳኔ የሚሽር ውሳኔ የሰጠው ጥር 20 ቀን 2000 ዓ.ም በነበረው ችሎት ሲሆን፣በሌላ በኩል ደግሞ መጋቢት 15 ቀን 2000 ዓ.ም መዝገቡን በማስቀረብ ሌላ ትእዛዝ ሰጥቶአል፡፡ ትእዛዙም እንዳየነው "....ቀደም ሲል የተሰጠው ውሳኔ እንደተጠበቀ ሆኖ የቀድሞ ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ግ ቁ. 208 አስተካክለናል፡፡ ተጠሪዎች ጉዳያቸውን በአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 142/1/ መሰረት ለአስማሚ እንዲያቀርቡ ብለናል፡፡ የሚል ይዘት ያለው ነው፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚሁ ላይ ነው፡፡

በበኩላችንም አመልካች ሚያዝያ 17 ቀን 2000 ዓ.ም በፃፈው ማመልከቻ ያቀረበውን አቤቱታ መሰረት በማድረግ ተጠሪዎችን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው የከፍተኛው ፍ/ቤት

በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 208 መሰረት የተደረገ እርማት ነው፤ በሚል የሰጠውን ትእዛዝ አግባብነት ለመመርመር ነው፡፡ በዚህ መሰረትም ይህን ነጥብ ከግራ ቀኝ ወገኖች ክርክር፣አቤቱታ ከቀረበበት ውሳኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

እንደምንመለከተው ተጠሪዎች ክስ የመሰረቱት በሕጉ መሰረት ሊከፈለን ሲገባ ሳይከፈለን ቀርቶአል ያሉትን የበረሐ አበል እንዲከፈላቸው ሲሆን፣የወረዳው ፍ/ቤትም ሊከፈል አይገባም በማለት ከአመልካች የቀረበውን የመከላከያ ክርክር ባለመቀበል የተጠየቀው የበረሐ አበል መጠኑን ጭምር በመግለጽ እንዲከፈል ወስኖአል፡፡ አመልካች ለከፍተኛው ፍ/ቤት በይግባኝ ያቀረበውም አበሉ እንዲከፈል መወሰኑ ትክክል አይደለም በማለት ነው፡፡ ከዚህ የተነሣም የከፍተኛው ፍ/ቤት አበሉ ሊከፍል ይገባል ወይስ አይገባም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን ከመረመረ በኋላ የተጠየቀው አበል አይከፈልም በማለት ግልጽ የሆነ ውሳኔ ሰጥቶአል፡፡ በወረዳው ፍ/ቤት ተሰጥቶ የነበረውን ውሳኔም ሙሉ በሙሉ ሽሮአል፡፡

የክርክሩ መነሻ በአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁ. 377/96 መሰረት የሚታይ የስራ ክርክር ሲሆን፣የሚመራውም በፍትሐብሔር ሥነ-ሥርአት ሕጉ እና አግባብ ባላቸው የአዋጁ ድንጋጌዎች መሰረት ነው፡፡ በአዋጅ አንቀጽ 138 እንደተመለከተው በመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የስራ ክርክር ችሎት የተጀመረ የስራ ክርክር ውሳኔ ካገኘ በኋላ በይግባኝ የሚታየው በይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት የስራ ክርክር ችሎት ነው(የአዋጁ አንቀጽ 139) በመደበኛው የስራ ክርክር ሂደትም ይግባኝ ሰሚው የስራ ክርክር ችሎት የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ ነው የሚሆነው፡፡ ይህ ችሎት በሰጠው ውሳኔ ቅሬታ ያለው ተከራካሪ ወገን ከዚህ በኋላ አቤቱታውን ሊያቀርብ የሚችለው ለሰበር ችሎት ነው፡፡ ከዚህ ውጪ በሆነ ሁኔታም ውሳኔው ሊለወጥ ወይም ሊሻሻል አይችልም፡፡ ይህ እንግዲህ አጠቃላይ ሂደቱ(ስርአቱ) ሲሆን፣ውሳኔውን በመቃወም ወደ በላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ለማለት ወይም አቤቱታ ለማቅረብ የሚፈልግ ተከራካራ ወገን ውሳኔውን በሰጠው ፍ/ቤት ሊታረም የሚገባ ወይም የሚችል ስህተት አለ ብሎ ካመነ ወደ በላይ ፍ/ቤት አቤት ከማለቱ በፊት ውሳኔውን ለሰጠው ፍ/ቤት አቤቱታ የሚያቀርብበት ስርአት እንዳለም ይታወቃል፡፡ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 208 ጥያቄ የሚነሳውም እዚህ ላይ ነው፡፡

የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 208 ርእሱ እንደሚያመለክተው "ስህተትን ስለማረም" በሚል የተደነገገ ነው፡፡ በዚህ ድንጋጌ መሰረት አቤቱታ የቀረበለት ፍ/ቤት (ውሳኔውን የሰጠው) ሊያርም ወይም ሊያስተካከል የሚችለው በሰጠው ውሳኔና ትእዛዝ ላይ የአፃፃፍ ስህተት፣የቁጥር አፃፃፍ ጉድለት ወይም ያልታሰበና ባለማስተዋል የተዘለለ ድንገተኛ የቃል ስህተት መኖሩን ካረጋገጠ ብቻ ነው፡፡ ይህ ደግሞ ግልጽ ነው፡፡ በክርክሩ ዋነኛ ጭብጥ ላይ አከራክሮ የሰጠውን ውሳኔ ስህተትን ማረም በሚል ሊያሻሽል ወይም ሊለውጥ አይችልም፡፡ በያዝነው ጉዳይ እንደምናየው የከፍተኛው ፍ/ቤት ውሳኔ የሰጠበት ክርክሩ ዋነኛ ጭብጥ ተጠሪዎች የጠየቁት የአበል ክፍያ ተገቢነት ያለው ነው ወይስ አይደለም የሚል ነው፡፡ ይህም ፍ/ቤቱ ከመረመረው በኋላ ጥያቄው ተገቢነት የለውም የሚል ውሳኔ ሰጥቶበታል፡፡ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 208 የተመለተውን ድንጋጌ መሰረት በማድረግ በኋላ የሰጠው ትእዛዝ ግን ከጉዳዩ ጋር በፍጹም የሚገናኝ አይደለም፡፡ ከተጠቀሰው ቁ. 208 ድንጋጌም ጋር የሚገናኝ አይደለም፡፡ ፍ/ቤቱ ከመጀመሪያውኑ ሊያስተናግደው የሚገባ አልነበረም፡፡ ስለዚህም በዚህ ረገድ የሰጠው ትእዛዝ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. አቤቱታ የቀረበበት በአፋር ብ/ክ/መ/የዞን አንድ ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 0974 መጋቢት 15 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ተሽሮአል፡፡
2. ወጪና ኪሣራ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ